# የላስ ቬጋስ ኢትዮጵያዉን ቅንጅትን ለመደገፍ ዳግም ቁርጠኝነታቸዉን አረጋገጡ !

ኢንጂነር ሃይሉ ሸዋል የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሊቀመንበር፣

> *"መታሰር በረጅም ግንብ የተሰራ ጊቢ ዉስጥ መቀመጥ ብቻ አይደለም። አንድ ሰዉ በነጻነት መናገር መጻፍ መንገድና መኖር ካልቻለ፤ የሚፈልገዉን የወረዳ የክልል የአገር መሪዎችን የመሻርና የመሾም መብቱን ከተነፈገ ያ ሰዉ እሥረኛ ነዉ"*

እንዳሉት በአሁኑ ወቅት በቃሊቲ የታሰሩ የሕዝብ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ መላዉ ነጻነት ፈላጊ ኢትዮጵያዊ በሙሉ እሥረኛ ነዉ። ከወህኒ ቤትም ለመዉጣት በቅንጅት መሪነት ሕዝቡ ለነጻነቱና ለመብቱ የሚያደርገዉን ትግል አጧጥፎታል።

የቅንጅት ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መርህዎቹም ከአሁን በኋላ በኢትዮጵያ የሚነሱ አለመግባባቶችን በጠመንጃ የመፍታት ባህል ተቀባይነት እንደማይኖረዉ የሚገልጹና ለዘመናት በድህነትና በጦርነት ሲንገላታ ለኖረዉ ሕዝባችን ብሩህ ተስፋን የሚሰጡ ናቸዉ።

የቅንጅት ሃይል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍና ፍቅር የመነጨ እንደሆነ ቢታወቅም ገዢዉ ፓርቲ ግን በሕዝብና ሕዝብ በመረጠዉ ቅንጅት ላይ እኩይ ዘመቻዉን ከፍቷል። የሕዝቡን ድምጽ ለማፈን ቀንና ሌሊት ደክሟል። በልመና ያገኘዉን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ከሕዝቡ አፍ እየነጠቀ የዲሞክራሲ ሃይሎችን ለመደምሰስ መንዝሯል። በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የሚኖሩትን የቅንጅት ደጋፊዎች ለመከፋፈልና ለማሰር ረጅም ገመድ አዘጋጅቶ በርካታ ከፋፋይ ሙከራዎችን አድርጓል።

ነገር ግን የቅንጅት ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንዳሉት "ቅንጅት በሕዝብ ልብ ዉስጥ የሚኖር መንፈስ ነዉ"። ቅንጅት ከመቼዉም የበለጠ ጠንክሯል። መሪዎቹም አገር አቀፍ "ጀግኖች" እየሆኑ ናቸዉ። ኢሕአዴግ ቅንጅትን ለማሰር የዘረጋዉ ረጅም ገመድ የራሱን አንገት እያነቀዉ ለሞት እያዘጋጀዉ ነዉ።

ለዚህም ምስክር እንዲሆን በፌብሩዋሪ 28 2007 በላስ ቬጋስ የተደረገዉን ሕዝባዊ ስብሰባ እንደ አንድ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። በዚህ ስብሰባ የሰሜን አሜሪካ አስተባባሪ ኮሚቴ የዘረጋዉን የአንድ ሚሊዮን ዶላር የማሰባሰብ ፕሮጀክቱን ለላስ ቬጋስ ነዋሪዎች ባስተዋወቀበት ጊዜ በአንድ ቀን 15,000$ ለማሰባሰብ ትችሏል።

አቶ አክሎግ ልመንህ የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ሊቀመንበርና አቶ ብርሃነ መዋ የቅንጅት የአለም አቀፍ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ ትግሉ የጥቂቶች ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደሆነና በተለይም የኢሕአዴግ አፈና በጨመረበት በአሁኑ ወቅት ዝም ብሎ የሚያይ ኢትዮጵያዊ ሊኖር እንደማይገባው አሳስበዋል። በላስ ቬጋስ የታየውም ሕዝባዊ ድጋፍ በሌሎች እህት የቅንጅት ማህበራት እንደሚቀጣጠልም ያላቸውን ጽኑ እምነት ገልጸዋል።

በዚሁ ጊዜ የላስ ቬጋስ የቅንጅት ደጋፊች ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አመራራቸውን ሲመርጡ የሕዝብ መሪዎች ከቃሊቲ እሥር ቤት አለ አንዳች ቅደመ ሁኔታ ወጥተው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነትን አየር እስኪተነፍስ ድረስ መከፈል ያለበትን መሰዋትነት እንደሚከፍሉ በኢትዮጵያዊነት ስሜትና ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል።

ኢትዮጵያ በአንድነቷና በነጻነቷ ኮርታ ለዘላለም ትኖራለች !